## *ወያኔን የምንቃወመው ለምንድነው?*

*እውን ባማራው ህዝባችን ላይ ወያኔ እያደረሰ ላለው ግፍ መፍትሄው ‘ሞረሽ’ ነው?*

*ወያኔን የምንቃወመው አቶ መለስ ትግሬ ስለሆኑ አይደለም። ቅንድባቸው ስለበዛና ቁመታቸው ስላጠረም አይመስለኝም። ቅንድባቸውም ቢሆን እኮ ተዘፍኖለታል። እንደሚባለውማ በየማለዳው ወደ ‘ሥራ’ ከመሄዳቸው በፊት ለባብሰው መስተዋት ፊት ለፊት ቆመው ራሳቸውን ሲታዘቡ ባለቤታቸው ወ/ሮ አዜብ አጠገባቸው ቆመው መለስ በመስተዋት ውስጥ የሚይዩትን ምስል እያዩ ‘ቁርጥ’ ጆርጅ ክሉኒን’ ይሏቸዋል አሉ። ለልጆቼ ት/ቤት ወርሃዊ ክፍያ የማሚላው በመከራ ነው ማለት የደፈሩ ሴት ይህን አይሉም ማለት አይቻልም። ደሞስ መንጌን አይተን የለ? ምንም እንኳ ወ/ሮ ውባንቺ ማን ብለው ያሞካሿቸው እንደነበር መናገር ባይቻልም። ጆምስ ብራውንን እንደማይሏቸው ግን በርግጠኝነት መገመት ይቻላል። ምነው ባገሩ የ‘መልከ መልካም’ ወንድ ምሳሌ ጠፍቶ ነው ባህር ማዶ ጉዞ ያስፈለገው ለሚለኝ መልሴ ለ ’ጀግኖቻችንም’ ምሳሌ የምንፈልገው ከባእዳን የመሆኑ አባዜ ተጠናውቶኝ ሳይሆን ይቀራል? ነው። ለነገሩ እኔን ብታዩኝ ደግሞ (ደግነቱ አንተያይም እንጂ) የድሮ የደርግ ሹምባሾች መንግሥቱ ከመለስ ‘መሻሉን’ ሲገልፁ ሊሉን እንደሚፈልጉት ‘ማረኝ መንጌ’ ትሉ ነበር። ደሞስ መንጌም ቢሆን እኮ ባንዲት የኢሰፓ ካድሬ ‘አከላት መንግሥቱ ተብሎ ተዘፍኖለታል’  ካልዘነጋችሁት። ሆዳም አማሮችም (ወያኔዎች ናቸው) ቢያዩኝ ‘መለስ ጂግናው ይግዛኝ’ እንደሚሉ እርግጠኛ ነኝ። ውጫዊ ገፅታ ማንነትን ማወዳደሪያ ሊሆን አይችልም ለማለትም ነው። ተግባራቸው ለህዝብ በጎ ሁኖ ገፅታቸው ከዚህም በከፋ! (ግን ‘መልከ መልካም’’ ራሱ ምንድነው?) ወደ ዋናው ቁም ነገር ልመልሳችሁ።*

*ወያኔን የምንቃወመው በተደራጀ የዘረኝነት ፖለቲካ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እያወደመ ስለሆነ ነው። ሰሞኑን በአማራው ህዝባችን ላይ እየወረደ ባለው ሰቆቃ የተቆጩ ወገኖች ችግሩን ለመከላከልና መፍትሄም ቢሆን በሚል ‘ሞረሽ’ የተሰኘ ድርጅት መመስረታቸው እየተሰማ ነው። ይሁን እንጂ በዘር መደራጀቱና የተናጥሉ ትግል እውን የተናጥል መፍትሄ ያመጣ ይሆን? በዘር የተደራጀውን ወያኔን እያወገዝንና እየታገልነው ነው እያልን የዚህኑ ልንጥለው የምንፈልገውን ከፋፋይ መንገድ መከተሉስ ከራስ ጋር መጣላት አይሆንም?*

*የሀገራችንን ፖለቲካ በተመለከተ አንድ አብዛኞቻችንን የሚገልፅ ባህርይ ቢኖር አመለካከታችን መርሃዊና (ፕሪንሲፐልድ) እርስ በርሱ የማይጣረስ (ኮንሲስተንት)  ያለመሆኑ ነው። የመለኪያ ሚዛናችንም የተዛባና (ደብል ስታንዳርድ) አድሏዊነት የሚንፀባረቅበት ነው። ላንዱ ጥፋት የተዘጋው አይናችን ለሌላው ይበረገዳል። የምንደግፈው ቡድን የሚሰራው ግፍ ቢያንስ ይደበቅለታል ባብዛኛው ግን ምክንያት ይፈለግለታል ከተጠያቂነት ነፃ ለማድረግ። ችግሩ የሀገርና የህዝብ ጉዳይ ባይሆን ብዙም ባላሳሰበ። ሰሞኑን ኦነግ ‘ነፍጠኛና’ ‘አማራ’ ሆናችሁ ለምን ተፈጠራችሁ ብሎ ከሻቢያና ከወያኔ ጋር ተባብሮ በገሀድ በህዝባችን ላይ ያካሄደውን የፍጅት ወንጀል ለመደበቅ በግንቦቴዎች እየተካሄደ ያለውን አሳፋሪ ድራማ ማስታወሱ በቂ ነው።*

*የቅርቡን ጊዜ የሀገራችንን ፖለቲካ እንኳ ብንመለከት ወያኔን ከምድር ገፅ እናጥፋው የሚሉ በሀገራቸን እየወረደ ባለው ግፍ አንጀታቸው የተቃጠለ ኢትዮጵያውያን ከሌላው ወያኔ ማለትም ኦነግ ከሚሉት ወንጀለኛ ፀረ ኢትዮጵያ ድርጅት ጋር ሲተቃቀፉ ማየት በራሱ አሳዛኝ ከመሆኑ በላይ አመለካከታቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚሰጡት የሀሰት ምክንያት እንዲሁ ያስገርማል።  እኔ እዚህ ላይ የ ኦነግን ምንነት በመዘርዘር ላደርቃችሁ አልፈልግም። ኦነግ አዲስ ፕሮግራም አለው፣ ተለውጧል፣ ሊሉን ለሚሞክሩ ግን እፈሩ ብዬ ከማለፍ ውጭ የምለው የለኝም። (ወያኔን ጣሉልኝና ኤርትራ የተገነጠለችበትን የሻቢያን አይነቱን ሬፈረንደም ላካሂድ የሚልን ቡድን መርዳት ኢትዮጵያን ማዳን ከቶም ሊሆን አይችልምና)። ይህን ባላችሁበት ቅፅበት ግን ወያኔን እየታገልኩ ነው ብትሉ ጊዜያችሁን ለሌላ ቁምነገር ብታውሉት ይበጃል ከማለት ውጭ እናንተን ለማሳመን ደፋ ቀና ማለቱን አልደፍረውም። ምናልባትም ኦነግ በሻቢያና ባንዳንዶች ርዳታና ደላላነት አራት ኪሎ ገብቶ ወያኔ እያፈራረሳት ያለችውን ሀገር እስከወዲያኛው ድራሿን ሲያጠፋት ይሆናል የምትባንኑት። ሁሉ ነገር ካለፈ በኋላ ማለት ነው። ግንቦቴዎች ማሳመኛ ነጥብ ሲያልቅባቸው ዝም ብሎ ቁጭ ከማለት ቢሞከር ምናለበት? ይሉናል የሀገር ጉዳይ ባይሆን ምንኛ በሳቅን። ኢትዮጵያ ማብቂያ የሌለው የህብረተሰብ ሳይንስ ቤተ ሙከራ (ሶሺያል ኤክስፐሪመንት) ማዕከል???*

*ወያኔን የምንቃወመው ለምንድነው???*

በፖለቲካው አለም የምንወስደው እያንዳንዱ እርምጃ በህ/ሰቡ አስተሳሰብና ስነ ልቡና የሚፈጥረው አንድምታ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም። ህዝባችንን ላለፉት ሀያ አመታት ፍዳውን እያስቆጠረ አበሳውን እያሳየ የሚገኘው የተደራጀ ዘረኝነት ነው። ዘረኝነት በመሰረቱ አንድን ህዝብ (ባንድ ዘር ሽፋን ሊሆን ይችላል) ኢላማ የሚያደርግ የብዝበዛና የእመቃ እኩይ የፖለቲካ መስመር ነው ማለት ይቻላል። ምናልባትም በስሙ ግፍ ከሚፈፀምበት የህዝብ ክፍል ጋር ምንም ግንኙነት ላይኖረው ይችላል። ይሁን እንጂ ዘረኛ ሥርአት የዕድሜ መሰረቱና ዋስትናው ህዝብን ባንድ ወይም በሌላ መንገድ መከፋፈል ነውና የግድ አንድን ዘር ተጠግቶ ሌላኛውን ዘር ወይም ዘሮች ኢላማ ማድረግ አለበት። ወያኔ ማንንም ሲገድል ኢትዮጵያዊ ስለሆነ ነው የገደልኩት አይልም 'ነፍጠኛ' 'አማራ' ...ብሎ እንጂ። ኦሮሚኛ ተናጋሪዎችን ሲገድል ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ኦሮሚያ ስለሆናችሁ ብሎ ነው። ወያኔ ይህን ግፍ በኢትዮጵያ ስም የሚያካሂደው ኦሮሚኛ ተናጋሪው ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያዊነት ላይ ቂም እንዲያረግዝና በረጅሙ ለታሰበው ህዝብን የመበታተን አላማ ሁኔታውን ለማመቻቸት ነው። ኦነግ ነኝ የሚለው ሌላው ዘረኛ ደግሞ 'ነፃ' አወጣችኋለው ለሚላቸው ወገኖች ወያኔ ገደላችሁ ሳይሆን ኢትዮጵያውያን ገደሏችሁ ብሎ ለመነገጃና ለመበታተኛ ይጠቀምበታል። ዘረኞች ግፍን ይዋዋሳሉና። እውነቱ ግን ወያኔ አባዱላን ኦሮሞ ስለሆነ ፤አዲሱ ለገሰን አማራ ስለሆነ አልገደላቸውም። ጋይምን ትግሬ ስለሆነም አልማረውም። ወያኔ የሚገድለው በያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሰማእትና ሰለባ ውስጥ ያለውን ኢትዮጵያዊነት ነው። አዲሱም ሆነ አባዱላ ወያኔ እንጂ ኢትዮጵያዊ አይደሉም።

ይህ ሲባል ግን 'አማራውን' ዒላማ ያደረገ ፍጅት በገፍ መካሄዱን በመዘንጋት አይደለም። የአማራው ፍጅት ራሱ መነሻው በዘር ድርጅት የተመራ ዘረኛ ፖለቲካ መሆኑን ለማሳየትና ይህን የግፍና የፍጅት ጎዳና ለመቀልበስ መፍትሄው 'ሞረሽን' መመስረት፣ በዘር መደራጀት ያለመሆኑን ለመግለፅ እንጂ። የዘረኝነት ዋነኛው ሰለባ ነኝ የሚል ስብስብ ይህንኑ የፍጅት ጎዳና ተምሳሊቶች አርአያ አይከተልም። ለዚህ ቁሻሻና ግፈኛ ጎዳናና ፀረ ኢትዮጵያ መርዝ ብቸኛው ማርከሻ የዘርኝነትን የመርፌ ቀዳዳ ሳይቀር መድፈን ነው። በያንዳንዷ ርምጃ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ አድርጎ መያዝ ነው።

አንድ ሰብሰብ በዘር በተደራጀ ቅፅበት ሌሎችን አግልሏል ወይም ሌሎች ራሳቸውን ከዚህ የተደራጀ ቡድንና በስሙ ከሚጠሩት አባላቱ ያገላሉ። ይህ የሁሉም የዘር ድርጅቶች እውነታ ነው። እያንዳንዱ ዘር የተደራጀበት የየራሱ (ማጠየቂያ/ጀስቲፊኬሽን) ቢኖረውም በህዝብ አብሮነት ላይ የሚፈጥረው የመለያየት ስሜትና በዘረኛ ድርጅቱ አማካይነት ሀገርን እያመሰ ላለው ሥርአት የሚሰጠው ጥቅም ግን ተመሳሳይ ነው። ያበራሽን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም እንዲሉ ወያኔን እየተቃወምን ኦነግን ከደገፍን፣ ያማራውን መደራጀት እየተቃወምን የግንቦትን የኦነግ ደላላነት ካልተጠየፍን፣ (ኮንሲስተንት ካልሆንን) በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ወይንም ከወገንተኝነት ቁጭትና ስሜት የተነሳ በእያንዳንዷ ርምጃችን የዘረኝነትን ቫይረስ ሊቀፈቅፍ የሚችል የወያኔ ወጥመድ ውስጥ ከወደቅን ተጠቃሚው ወያኔ ብቻ ነው።

ባማራው ህዝብ ስም ለሆነ አላማ ደርጅት መፍጠር የሚጠቅመው ወያኔን ብቻ ሳይሆን አሁን በሻእቢያ ተገንነት በኦሮሞ ህዝብ ስም ተረኛ ወያኔ ለመሆን እየተዋደቀ ያለውን ፀረ ኢትዮጵያውን ኦነግንም ነው። አንዳንዶች አማራው ቢደራጅም የሌሎችን ጥፋት አይደግምም፣ በኢትዮጵያዊነቱ አይጠረጠርም ... ሌላም ሊሉ ይችሉ ይሆናል። ሀሰትም ላይሆን ይችላል። ችግሩም ይኸው 'አማራ' የተባለው መጠሪያ በኢትዮጵያ ወዳጆችም ሆነ ጠላቶች አስተሳሰብ ውስጥ የተሰጠው ከፍተኛ ግምትም ነው። በዚህ ከፍተኛ ግምት በተሰጠው ስብስብ (ማንና ከ እስከው የት ድረስ እንደሆነ መገመት ቢከብድም) ስም መደራጀት የስብስቡን ታሪክና ሚና ማውረድም ይሆናል። ይህ ስብስብ ከተደራጀ ማን አይደራጅ? ማንስ በዘር በመደራጀቱ ይወቀስ? በአማራው ስም መደራጀት በስሙ ድርጅት ለተፈጠረበት ስብስብ ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ በስሙ ሰበብ ኢትዮጵያን እያወደመ ላለው ወያኔና ለመሰሉ ኦነግ የሚሰጠው ፖለቲካዊ ጥቅም በእጅጉ ይበልጣል። ከዚህ ቀደም የተደራጀው የአማራው ድርጅት የአማራውን ስቃይ ከመዘገብ ያለፈ የሰራው ይህ ነው የሚባል ነገር ያለ አይመስለኝም ( በወያኔ ሥር 'ህጋዊ' ትግል አካሂዶ የትም መድረስ አይቻልምና)። በድርጅቱ ሥም የግል ጥቅማቸውን ካሳኩት ብልጣ ብልጦችና ድርጅቱን ለወያኔ ስለላ ሥራቸው በሽፋንነት ከተጠቀሙበት ልደቱን አይነት ወያኔዎች በስተቀር። ያንድ ዘር ትግል ወይም ባንድ ዘር ስም የሚካሄድ ትግል በስሙ ትግል ለተካሄደበት የህዝብ ክፍል የተገባለትን 'ለውጥ' ማምጣት ቢችል ኖሮ የትግሪኛ ተናጋሪ ተወላጆችና በሻቢያ ቁጥጥር ሥር በዋለው የህ/ሰብ ክፍል ያሉትን በጠቀመ ነበር።

የመለስን አውዳሚ የዘር ድርጅት ተቃውመን ያማራውን በተናጥል መደራጀት ከደገፍን (ልዩነቶቹ እንደተጠበቁ ሆነው) ብዙም መጓዝ አንችልም። ያማራውን ድርጅት መመስረት እየኮነንን የኦነጉን ደላላ ግንቦት ሰባትን ከደገፍንና ከታገስን የፀረ ወያኔው ትግላችን ጥያቄ ውስጥ እንደገባ ብቻ ሳይሆን ከወዲሁ እንደተኮላሸ ማወቅ አለብን። ወያኔን ለምንድነው የምንቃወመው?

ፖለቲካና ሞራሊቲ ባንድ አልጋ ላይተኙ ይችላሉ ነገር ግን ወያኔን ተጠይፎ ኦነግን ማቀፍ፣ ኦነግን ኮንኖ ያማራውን ድርጅት ማዋቀር የሞራል ማማ ላይ አያወጣም ተአማኒነትንም ያሳጣል። የሀያ አመቱ ልምድ እንዳሳየንም በጎጥ መደራጀት በመጨረሻ የሀገርና የህዝብ ዕጣ ፈንታ ላይ ተጨማሪ መከራ ከመሆን አልፎ በፀረ ወያኔው ትግል ላይ ደንቃራ መሆንም ነው።

ኢትዮጵያ ከወያኔ ዘረኛ ሥርአት ተላቃ ሁሉን አሳታፊ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት መመስረት ሲቻል ብቻ ነው እያንዳንዱ ስብስብም ሆነ ግለሰብ ነፃ የሚወጣውና የተናጥሉን ትግል በአንድነቱ ትግል ተክተን ማለቂያ ለሌለው የዘር/የቡድን 'ነፃነት' ሳይሆን ለዘላቂ የግለሰብ ነፃነት፣ የህዝብና የሀገር ትንሳኤ እንነሳ።

ኢትዮጵያዊነት ለዘላለም ይኖራል!